INTERME

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ማ/ቅ/ጽ/ቤት
EHTIOPIAN REVENUE AND CUSTOMS
AUTHORITY
A.A. KAIITY CUSTOMS BRANCH OFFICE

የውስጥመጻጻፊ

ቁጥር፡ ም/ሥ/ጉ/ጉ/00383/10
ቀን፡ 10/09//2010

- ለጉምሩክ ስነ ስርዓት አፈፃፀም የስራ ሂደት
- ለህግ ማስከበር የስራ ሂደት
- ለደንበኞች አገልግሎት የስራ ሂደት
- ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የስራ ሂደት
- ለቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ጉ/ስ/ስ/አ/ስራ ሂደት
- ለኢስተርን ኢንዱስትሪ ዞን ጉ/ስ/ስ/አ/ስራ ሂደት
- ለገላን ተርሚናል ጉምሩክ ማስተባበሪያሽ
- ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
- ለመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመ/የተ/መ/ቡድን

- ከ፡ ጉምሩክ ጉዳዮች ም/ስራ አስኪያጅ
  <u>አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

ገ/እግዚአብሔር ገ/ጻድቅ
የጉምሩክ ጉዳዮች ም/ስራ አስኪያጅ
G/EGZIABHER G/TSADK
CUSTOMS AFFAIR DEPUTY
MANAGER

የዋና መ/ቤት የጉምሩክ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በቁጥር 4.1/184/10 ግንቦት 06/2010 ዓ.ም. በፃፈው ደብዳቤ ከውጪ ገብተው ለሸማቹ ህብረተሰብ በሚከፋፈሉ የፓልም ዘይት፣ ስኳርና ስንዴ ላይ የስካኒንግ ክፍያ እንዳይጠየቅ የተላለፈው መመሪያ አሁንም ጸንቶ ያለ እና ተለዋጭ መመሪያ እስካልተላለፈ ድረስ ተፈፃሚ ሆኖ እንደሚቀጥል በቁጥር ገ/ኢ/11/1/367 በቀን 02 ግንቦት 2010 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ያሳወቀ መሆኑን የገለፁልን ስለሆነ ለተገቢው አፈፃፀም ይረዳ ዘንድ የተላከውን 7 ገጽ ደብዳቤ በአባሪነት አያይዘን ልከንላችኋል።

ከሰላምታ ጋር

<u>ግልባጭ፣</u>
- ለሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
- ለም/ስራ አስኪያጅ /ህግ ማስከበር ዘርፍ/
  <u>አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

ሐ) የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እስከአሁን እየተጠየቀ ካለው የInsurance አገልግሎት ክፊሉን ብቻ ማለትም 50% ብቻ እንዲያስከፍል፣

መ) የሸቀጦቹ አስመጪዎች የሆኑት ሦስቱ መንግሥታዊ የልማት ድርጅቶች (ስኳር ኮርፖሬሽን፣ ጅንአድ እና እህል ንግድ ድርጅት) የመጫኛና ማውረጃ፣ ሌሎች ወጪዎች (Loading & Unloading Charges, as well as Other handling expenses) በልማት ድርጅቶቹ የየራሳቸው ገቢ እንዲሸፈን፣

ሠ) የመጋዘን ክፍያና የኮንቴይነር ዲመሬጅ (Container Charges + Container Demmurage) ክፍያ ሲያጋጥም ከሚጠየቀው ክፍያ ሩቡን (25%) የኢትዮጵያ ባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት፣ ግማሹን (50%) የየሸቀጦቹ አስመጪ የልማት ድርጅቶች እንዲሸፍኑት መወሰኑን እያስታወቅን፣ በአፈጻጸም ረገድ ችግር ከጋጠማችሁ ሥራውን በቅልጣፊ የመምራቱ ተግባሩ ሳይተጓጐልና ከፍ ሲል የተጠቀሰው የአገልግሎት ክፍያ ሳይለወጥ ጥያቄዎቻችሁን በጽሑፍ ለማቅረብ የምትችሉ መሆኑን እናሳስባለን:: ለአፈጻጸም እንዲረዳችሁ የአገልግሎት ክፍያ ማሳያ ሠንጠረዥ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ መላኩን እንገልፃለን::

ከሰላምታ ጋር

ሶፊያን አህመድ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣
- ለኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት
- ለሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት
- ለስኳር ኮርፖሬሽን

አዲስ አበባ

ስልክ Tel. 55 24 00
ፖ.ሣ.ቁ P. O. Box 1905
ፋክስ Fax 55 13 55, 55 14 96
አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ Addis Ababa, Ethiopia

<u>የወጪ ዝርዝር ሥራ ላይ ያለው የአገልግሎት ክፍያ ተመንና ማሻሻያው</u>

| ተ.ቁ | Cost Particulars | ሥራ ላይ ያለ ተመን | ማሻሻያ / ሥራ ላይ ሊውል የታሰበ ተመን | የአገልግሎት ክፍያ ሰብሳቢ ድርጅት ስም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Insurance | (FOB +10%)*0.49% | (FOB +10%) * 0.245 (ቀደም ሲል ሲፈጸም ከነበረው ከፊሉን ብቻ ማስከፈል) | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት |
| 2 | Bank Charge | 2.5% of FOB Value (1.5% National Bank + 1.0% Commercial Bank) | አይከፈልም | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና የንግድ ባንክ |
| 3 | Bank Interest | 9.5% | • ለጅንአድና ስኳር ኮርፖሬሽን ዝቅተኛ ተቀማጭ ወለድ ብቻ፣<br>• ለኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት ወለድ የማይታሰብ | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ |
| 4 | Scanning Fee | CIf x0.07% | አይከፈልም | የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን |
| 5 | Quarantine | Birr 7.50/Ton | የማይከፈል | የምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን |
| 6 | Inspection fee | 0.26%of CIF value | የማይከፈል | የንግድ ሚኒስቴርና የተስማሚነት ምዘና ድርጅት |
| 7 | Storage charges at Djibouti port | USD11/container after 8 days | • ከክፍያው 25% የባሕር የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት<br>• ከክፍያው 50% የየሸቀጦቹ አስመጪ ድርጅቶች | የባሕር የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት፣ ሦስቱ አስመጪ የልማት ድርጅቶች |

| ተራ ቁ | Cost Particulars | ሥራ ላይ ያለ | ማሻሻያው ሥራ ላይ እንደዋለ የተወሰነ ተመን | የአገልግሎት ክፍያ ጠያቂ ድርጅት ስም |
|---|---|---|---|---|
| 8 | Container Demurrage | USD 6/ Container after 30 days | • ከክፍያው 25% የባሕር የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርጅት<br>• ከክፍያው 50% የየሽቀጦቹ አስመጪ ድርጅቶች ፤ | የባሕር የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎትና፣ ሦስቱ አስመጪ የልማት ድርጅቶች |
| 9* | Dry port charges | Rate varies | አይከፈልም | የደረቅ ወደብ አገልግሎትና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን |
| 10 | Loading & Unloading Charges | አስመጪ የልማት ድርጅቶቹ በየራሳቸው የሚሸፍኑት ይሆናል | በአስመጪ ድርጅቶቹ ይሸፈናል (ጅንአድ፣ ኢትዮጵያ እህል ንግድና ስኳር ኮርፖሬሽን) | |
| 11 | Handling Expenses | | | |

*9) Dry port charges:-

- Dry Port Charges ................................ Port dues Birr462/Container
- Terminal Handling ................................ Birr92 8 /Container
- Seal cating ................................ Birr 8 /Container
- Receipt interchange ................................ Birr 35/ container

Docomentation (B/L) ................................ Birr24/Shipment ያጠቃልላል፡፡